# ወርሓዊ ዜና ሚቲዎሮሎጂ

# Monthly Met. News








የአየር ጠባይ መረጃ ተጠቃሚነትንና ተደራሽነትን ለማጎልበት የተካሄደው መድረክ ተሳታፊዎች

## ቅጽ 4 ቁጥር 9 የሕዝብ ግንኙነትና ኮሙኒኬሽን ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት

መጋቢት 2010 ዓ.ም

## እያደገ ለመጣው የመረጃ ፍላጎት ምላሽ መስጠት የሚቻለው የአቅም ግንባታ ሥራዎችን ከማከናወን ጎን ለጎን ለመረጃ ተደራሽነት ቅንጅታዊ አሰራሮችን ማጎልበት እንደሚገባ ተገለጸ

ከመንግስታዊ ተቋማትና መንግስታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች ጋር ተቀናጅቶ መሥራት የአየር ሁኔታና ጠባይ መረጃዎችን ለአገልግሎቱ ተጠቃሚዎች ይበልጥ ተደራሽ ለማድረግና የህብረተሰቡን የመረጃ ተጠቃሚነት እውን ማድረግ ያለውን ጠቀሜታ በሚያሳይ ጥናታዊ ጽሑፍ ላይ ውይይት ተካሄደ፡፡

ጥናታዊ ጽሑፉ የቀረበው ብሔራዊ የሚቲዎሮሎጂ ኤጀንሲ ከክርስቲያን ኤይድ ጋር በመተባበር ኬር/BRACED ፕሮጀክት በመቅረፅ የአየር ጠባይ አገልግሎትን ባለፉት ሦስት ዓመታት ለአርሶ አደሩ ተደራሽ ለማድረግ ያከናወናቸው ሥራዎችንና በሂደቱም የተገኙ ውጤቶችንና ያጋጠሙ ተግዳሮቶችን በጥልቀት በመገምገም ለቀሪ ሥራዎች ትምህርት ሊሆኑ የሚችሉ እና ሊሻሻሉ የሚገቡ ጉዳዮችን በመለየት ተገቢውን ማስተካከያ ለማድረግ ታስቦ እ.ኤ.አ ከፌብራሪ 16-17 2018 በአዲስ አበባ ጌት-ፋም ሆቴል በተዘጋጀውና ከ80 በላይ ባለድርሻ አካላትን ባሳተፈ የምክክር መድረክ ላይ መሆኑ ታውቋል፡፡

የምክክር መድረኩን በንግግር የከፈቱት የኤጀንሲው ዋና ዳይሬክተር አቶ ፈጠነ ተሾመ በአየር ሁኔታና ጠባይ አገልግሎት ማሻሻል ላይ ትኩረት በማድረግ ባለፉት ሦስት ዓመታት ተግባራዊ ሲደረግ በቆየውና የአቅም ግንባታ ሥራዎችና የተገኙ ውጤቶችን ለመገምገም በተዘጋጀው መድረክ ላይ ከሀገር ውስጥና ከውጭ ሀገር በፕሮጀክቱ ሲሳተፉ ለቆዩ የዘርፉ ተመራማሪዎችና ባለድርሻ አካላት ምስጋና አቅርበዋል፡፡

ከጊዜ ወደ ጊዜ ከሚለዋወጠው የአየር ሁኔታና ጠባይ ጋር ተያይዞ በወቅቶች የዝናብ አገባብና አወጣጥ ላይ ከአየር ሁኔታና ጠባይ ጋር ተያይዞ አሉታዊ ተፅዕኖ እየፈጠረ መሆኑንና ከዚህም ጋር ተያይዞ ባልተለመደ ሁኔታ የደረቅ ሰሞናት የሚደጋገሙበት እና በአጭር ጊዜ ውስጥ ከባድ ዝናብ በመዝነብ ወደ ጎርፍ የሚለወጥበት በዚህም ምክንያት የግብርናው ዘርፍና ሌሎች ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ዘርፎች ለተለዋዋጩ የአየር ሁኔታና ጠባይ ተጋላጭ እየሆኑ መምጣታቸውን ገልፀዋል፡፡

ባለንበት ዓለም ከአየር ሁኔታና ጠባይ ተለዋዋጭነት ጋር ተያይዞ ሊከሰቱ የሚችሉ አደጋዎችን ለመቋቋምና ሊኖሩ የሚችሉ መልካም አጋጣሚዎችን በተሻለ መልኩ አሟጦ ለመጠቀም የአየር ሁኔታና ጠባይ ትንበያና የምክር አገልግሎት መጠቀም አዋጭነቱ አጠያያቂ እንዳልሆነ ዛሬ ላይ በከፍተኛ ሁኔታ መግባባት የተፈጠረበት መሆኑና በዚህም ምክንያት የአገልግሎቱ ተጠቃሚ ፍላጎት ባልተጠበቀ መልኩ እያደገ መምጣቱን ጠቅሰው ኤጀንሲውም መረጃዎችን በተሻለ መልኩ ለማቅረብ በርካታ ሥራዎችን በመሥራት ላይ ይገኛል ብለዋል፡፡

አቶ ፈጠነ በመቀጠል ኤጀንሲው አገልግሎቱን ለማሻሻል ከመንግስት ከሚመደበው በጀት በተጨማሪ በርካታ ፕሮጀክቶችን በመቅረፅ ከተለያዩ ተባባሪ አካላትና ለጋሽ ድርጅቶች ጋር ጠንካራ ትስስር በመፍጠር እየተሰሩ ያሉ ሥራዎችን አንስተዋል፡፡ ለአብነትም ከክርስቲያን ኤይድ ጋር ለሦስት ተከታታይ ዓመታት Climate information and Assets for Climate Resilience in Ethiopia (CIARE) የሚል ዓላማን ለማሳካት ሲተገበር የቆየውን ጠቅሰዋል፡፡

በፕሮጀክቱም አራት ዘመናዊ የሚቲዎሮሎጂ መረጃ መሰብሰቢያ ጣቢያዎችን፣ የባለሞያዎችን የትንበያ አቅም ለማሻሻል የሚያስችሉ ስልጠናዎችን፣ በመረጃው አስፈላጊነትና አጠቃቀም እንዲሁም በኤጀንሲው በየአሥር ቀኑ፣ በየወሩ፣ በየወቅቱ አጋማሽና በየወቅቱ መረጃው ለተመረጡ

ወረዳዎች በፍጥነት የሚደርስበትን ሁኔታ በማመቻቸት በኩል ውጤታማ ሥራዎችን ሲያከናውን መቆየቱን በመጥቀስ የተሰራው ሥራ ከባለድርሻ አካላትና ከአገልግሎታችን ተጠቃሚዎች ጋር ጠንካራ ትስስር እንዲፈጠር፣ ብሎም መረጃው በወቅቱ ተጠቃሚው ዘንድ እንዲደርስና ተጠቃሚነቱ እንዲያድግ ምክንያት ከመሆኑም በላይ ለኤጀንሲው ቀጣይ ሥራ መሠረት እንዲጣል ያደረገ መሆኑን አብራርተዋል፡፡

ለአንድ ቀን ከግማሽ የሚካሄደው የምክክር መድረክ የመንግስት መ/ቤቶችን፣ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን፣ ዓለም ዓቀፍና ሀገራዊ የዘርፉ ተመራማሪዎችን ያገናኘና በመረጃ ማምረት፣ ማሰራጨትና በዚህ ፕሮጀክትም ሆነ በቀጣይ ሥራዎቻችን ላይ መሻሻል ያለባቸውን ጉዳዮች በአግባቡ ለመለየትና ተገቢውን ማስተካከያ ለማድረግ ትልቅ እድል የሚፈጥር መሆኑን በመግለፅ የውይይት መድረኩ በይፋ መከፈቱን አብስረዋል፡፡

ክርስቲያን ኤይድን በመወከል መልዕክት ያስተላለፉት በኢትዮጵያ የክርስቲያን ኤይድ ዳይሬክተር አቶ ይጥና ተካልኝ በንግግራቸው በዓለም ዓቀፍ ደረጃ ከአየር ጠባይ መለዋወጥ ጋር ተያይዞ በአሁኑ ጊዜ የበረዶ መቅለጥ ባልተለመደ ሁኔታ ለበጎርፍ መጥለቅለቅ፣ ለረጂም ሰሞናት የውሃ እጥረት፣ ለድርቅ የመጋለጥ ሁኔታ እንዲሁም በዝናብ አገባብና አወጣጥ ላይም ከፍተኛ መዋዠቅ የሚስተዋልበት ሁኔታ መፈጠሩን ጠቅሰው፣ ከዚህ ጋር ተያይዞ የግብርና ሥርዓታችን እንዲሁም ሌሎች የኢኮኖሚ ሴክተሮች ለተለዋዋጩ የአየር ጠባይ በተደጋጋሚ ተጋላጭ መሆናቸውን ገልጸዋል፡፡ ስለሆነም በየግዜው እየጨመረ የሚመጣውን ጫና በመቋቋም ሀገራዊ ልማትን ማስቀጠል የሚያስችል አሠራር መዘርጋት፣ ብሎም ከአየር ሁኔታና ጠባይ ጋር ተያይዞ የሚመጡ ችግሮችን አስቀድሞ በማወቅና ለመቋቋም የሚያስችል የአደጋ ሥጋት መከላከል ሥርዓት መዘርጋትና መተግበር ያስፈልጋል በማለት ብሔራዊ የሚቲዎሮሎጂ ኤጀንሲ በዚህ ዙሪያ አስቀድሞ አስፈላጊውን የቅድሚያ ማስጠንቀቂያና የምክር አገልግሎትን በመስጠት ሊደርስ የሚችለውን አደጋ አስቀድሞ መከላከል/ መቀነስ እንዲቻል ከፍተኛ ሚና በመጫወት ላይ እንደሚገኝ ገልፃዋል፡፡

ከዚህ ጋር ተያይዞ ከኋላቀር የአስተራረስ ዜይቤ ያልተላቀቁ አርሶ አደሮችና አርብቶ አደሮች በየግዜው የሚከሰቱ የተፈጥሮ አደጋዎችን በራስ አቅም መቋቋም የማይችሉበት ሁኔታ በስፋት እንደሚስተዋል ጠቅሰው የኢትዮጵያ መንግስት እነዚህን ችግሮች ለመቋቋም የሚያስችሉ ሀገራዊ አቅም በመገንባት ችግሮቹ ከመከሰታቸው በፊት ከኤጀንሲው በሚደርሰው መረጃ መሠረት አቅዶ ጉዳት ከማድረሱ በፊት አፋጣኝ ምላሽ የሚሰጥበት ደረጃ ላይ መደረሱን ጠቅሰዋል፡፡

BRACED-CIARE ፕሮጀክት የተቀረፀው የአየር ጠባይ አገልግሎትን በማጠናከር፣ ወቅታዊና ጥራት ያለው የአየር ሁኔታ መረጃዎችን ለተጠቃሚው በተለይም ለአርሶ አደሩና ለአርብቶ አደሩ የህብረተሰብ ክፍል መስጠትን መነሻ ያደረገ ነው፣ በዚህም ውስጥ ብሔራዊ የሚቲዎሮሎጂ ኤጀንሲ የአየር ሁኔታና ጠባይ ትንበያ መረጃዎችን ለተለዩት የህብረተሰብ ክፍል በማቅረብ በኩል ከፍተኛ ሚና የተጫወተ ሲሆን ሌሎች ኤጀንሲው ባለድርሻ አካላት ደግሞ የባለሞያዎችን የመፈፀም አቅም በመገንባት ድጋፍ የማድረግ የአካባቢ ማህበረሰብና የመንግስት አስፈፃሚ አካላት በአገልግሎቱ ላይ የተሻለ ግንዛቤ እንዲኖራቸውና በአየር ሁኔታ መረጃ አጠቃቀም ዙሪያ የተሻለ ግንዛቤ በመፍጠር በመረጃ የበለፃገና በእውቀት ላይ የተመሠረቱ ውሳኔዎችን በመወሰን ከአየር ሁኔታና ጠባይ ጋር ተያይዞ የሚከሰቱ ተፅዕኖዎችን መቋቋም የሚችል ኢኮኖሚን ለመገንባት እንደ ሀገር ርብርብ መደረጉን አብራርተዋል፡፡

በመጀመሪያው ቀን የአየር ጠባይ አገልግሎትን ከማምረትና በተለየ መልኩ ለኬር ፕሮጀክት የሚውለውን የትንበያ ውጤት ከማመንጨት አንፃር የኤጀንሲው ሚና እና የተገኘውን ልምድ በተመለከተ ፅሁፍ ያቀረቡት አቶ አሳምነው ተሾመ የትንበያና ቅድመ-ማስጠንቀቂያ ዳይሬክቶሬት

ዳይሬክተር ሲሆኑ፣ የአየር ጠባይ አገልግሎትን ለማሻሻል የተሰጡ የአቅም ግንባታ ስልጠናዎችም ከውጭ በመጡ የዘርፉ ከፍተኛ ባለሞያ ቀርቦ ውይይት ተደርጎበታል፡፡ የአየር ሁኔታና ጠባይ ትንበያዎችን ወደ ህብረተሰቡ ተደራሽ ከማድረግ አንፃር የነበረውን ሁኔታ ያቀረቡት የኬር ፕሮጀክት ማኔጅንግ ዳይሬክተርና የBBC Media Action ተወካይ ወ/ት ዮዲት አክሊሉ ናቸው፡፡

የአየር ሁኔታና ጠባይ መረጃዎችን ተደራሽ ከማድረግ አንፃር የደቡብ ክልልና የኦሮሚያ ክልላዊ መንግስታት ሬዲዮና ቴሌቭዥን ድርጅቶች እንዲሁም በማሕበረሰብ ደረጃ መረጃን ተደራሽ በማድረግ ላይ የሚሰራ ሁንዴ የተባለው ድርጅት በነበረው የመረጃ ልውውጥ ዘዴዎችና የአየር ጠባይ መረጃ በአግባቡ ሥራ ላይ እንዲውል የተሰራው ሥራ፣ የተገኘው ልምድ በስፋት ቀርቧል፣

የአየር ሁኔታና ጠባይ መረጃን ከመጠቀም አንፃር በማህበረሰቡ በኩል የነበረውን ሁኔታ የያቤሎ ወረዳ አርብቶ አደርን በመወከል ጥናታዊ ፅሁፍ ቀርቧል፡፡ ሌላው በዕለቱ የቀረበው ጥናታዊ ፁሁፍ ከኤጀንሲውና በፕሮጀክቱ ከሚሳተፉ አካላት ውጭ ገለልተኛ በሆነ አካል በአገልግሎቱ አሰጣጥና አገልግሎቱ በአካባቢው ማህበረሰብ የእለት ተዕለት እንቅስቃሴና ምርታማነቱን ከማሳደግ አንፃር ያመጣውን ውጤት  በማጥናት ለመድረኩ ተሳታፊዎች አቅርበዋል፡፡ ሌላው የቀረበው በተመረጡ ወረዳዎች ሲሰጡ የነበሩ የቅድሚያ ማስጠንቀቂያና የምክር አገልግሎት ውጤቶችን በተጨባጭ መሬት ላይ (በአካባቢው በሚገኙ ጣቢያዎችና ለአካባቢው ማህበረሰብ በተሰራጩ መሣሪያዎች በመታገዝ) ከተሰበሰቡት መረጃዎች ጋር በማነፃፀር ያካሄዱትን የጥናት ውጤት ለተሳታፊዎቹ ያቀረቡት አቶ መለሰ ለማ ናቸው፡፡

በቀረቡት ጥናታዊ ፁሁፎች ላይ ተሳታፊዎች ጥያቄና የተለያዩ ሀሳቦችን በማንሳትና በጥያቄ መልክ ለተነሱ ጉዳዮች ተጨማሪ ማብራሪያ ተሰጥቷል፡፡

በዚሁ በሁለት ቀናት ዐውደ-ጥናት ላይ ተሳታፊዎቹ በአራት ቡድን በመመደብ ከመድረክ በተሰነዘሩት የመወያያ ሐሳቦች ላይ፣ ማለትም፡- የሚቲዎሮሎጂ ትንበያና የቅድሚያ ማስጠንቀቂያ የምክር አገልግሎትን ከማሻሻል አንፃር የተገኘው ልምድና በቀጣይ ሊሻሻሉ በሚገቡ ጉዳዮች፤ የሚቲዎሮሎጂ ትንበያና የቅድሚያ ማስጠንቀቂያ የምክር አገልግሎትን ተደራሽ ከማድረግ አንፃር በተገኘው ትምህርትና በቀጣይ መሻሻል ባለባቸው ጉዳዮች ዙሪያ፤ የሚቲዎሮሎጂ ትንበያና የቅድሚያ ማስጠንቀቂያ የምክር አገልግሎትን በአግባቡ ጥቅም ላይ እንዲውሉ ከማድረግ አንፃር የተገኙ ትምህርቶችና በቀጣይ ሊሻሻሉ በሚገቡ ጉዳዬች፤ የሚቲዎሮሎጂ ትንበያና የቅድሚያ ማስጠንቀቂያ የምክር አገልግሎት እንዲሻሻል የተለያዩ ሴክተር መሥሪያ ቤቶች፣ ባለድርሻ አካላትና ለጋሽ ድርጅቶች ከኤጀንሲው ጋር በቅንጅት ከመሥራት አንፃር የተገኘው ልምድና በቀጣይ በምን መልኩ አብረው መሥራት እንዳለባቸው በሚያመላክቱ ጉዳዮች ላይ ሰፊ ውይይት ማድረጋቸው ታውቋል፡፡ የቡድን ውይይቱ በተወካዮቻቸው አማካኝነት ወደ መድረክ ቀርቦ ሰፊ ውይይት ከተካሄደ በኋላ ቀጣይ አቅጣጫዎችን በማስቀመጥ የምክክር መድረኩ ተጠናቋል፡፡

# በብሔራዊ የሚቲዎሮሎጂ ኤጀንሲ የ2010 በጀት ዓመት የሰባት ወር ዕቅድ አፈጻጸም ላይ ውይይት ተካሄደ

የአንድ ቀን ውይይቱ የተካሄደው የካቲት 30 ቀን 2010 ዓ.ም ሁሉም የኤጀንሲው ሠራተኞችና አመራሮች በተገኙበት በኢትዮጵያ ሆቴል አዳራሽ መሆኑ ታውቋል፡፡

አቶ ፈጠነ ተሾመ የብሔራዊ ሚቲዎሮሎጂ ኤጀንሲ ዋና ዳይሬክተር በውይይቱ መጀመሪያ ላይ ባደረጉት አጭር መግለጫ፣ የዕቅድ አፈጻጸማችንን በመገምገም ደካማና ጠንካራ ጎኖችን ለይተን ለቀጣይ ሥራ አቅጣጫ የምንለዋወጥበት መሆኑን አመልክተዋል፡፡ ተሳታፊዎችም በሚቀርበው ሪፖርት ላይ ንቁ ተሳትፎ እንዲያደርጉና ነጻ ሆነው ሐሳባቸውን እንዲገልጹ አሳስበዋል፡፡

አቶ አሰፋ መኮንን የዕቅድና በጀት ዝግጅት፣ ግምገማና ክትትል ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር የሰባት ወሩን የቁልፍ፣ የመደበኛና ካፒታል ፕሮጀክቶች ዕቅድ አፈጻጸም ከግቦች አንጻር አቅርበዋል፡፡

አቶ አሰፋ በገለጻቸው ከግቦች አንጻር የተከናወኑትን ዋና ዋና ተግባራት ሲዘረዝሩ፣ ከቁልፍ ሥራዎች አኳያ የሪፎርምና ልማታዊ መልካም አስተዳደርን በማጠናከር ውጤታማ አገልግሎት በመስጠት የተገልጋዮችን ርካታ ከማሳደግ ግብ አኳያ በለውጥ ሠራዊት ግንባታ ረገድ የአንድ ለአምስት አደረጃጀት የውሎ ግምገማ፣ ሳምንታዊ ስብሰባ፣ የ15 ቀን የፕሮሰስ ካውንስል እንዲሁም በወርሃዊ የመላው ሰራተኛ ስብሰባ የክትትልና ግምገማ ስርዓቶች አልፎ አልፎ መቆራረጦች ቢኖሩም ተግባራዊ መሆናቸውን አመልክተዋል፡፡ የተቋማዊ ለውጥ አመራር እና የለውጥ ሠራዊት ግንባታ ሁኔታ፤ በለውጡ ስራ አመራሮች በስራቸው ያሉትን ፈፃሚዎች በአመለካከት፣ በክህሎትና በዕውቀት በማብቃት እንዲሁም በቁርጠኛነትና በባለቤትነት በመምራት ረገድ የሚከናወኑ ስራዎች፣ ማስተባበር ድጋፍ እና ክትትል ማድረግ፣ እንዲሁም ልማታዊ መልካም አስተዳደርን ስለማረጋገጥ የታቀዱት ሥራዎች ከሞላ ጎደል መከናወናቸውን ገልጸዋል፡፡

በበጀት ዓመቱ በተቋም ደረጃ የተለዩትን የኪራይ ሰብሳቢነት ምንጮችን ከማድረቅ ረገድ፡ የመንግስት የስራ ሰዓትን አለማክበር በስፋት የታየ ችግር መሆኑ በሪፖርቱ ተመልክቷል፡፡ ኤጀንሲው የአመራሩንና የፈፃሚዉን የአመለካከት፣ የዕውቀትና የክህሎት ክፍተት ለመሙላት በዋና መ/ቤትና በሚቲዎሮሎጂ ማዕከላት ያለውን የሰው ሃይል የአፈፃፀም ክፍተት መሰረት ያደረገ የስልጠና ፍላጎት ዳሰሳ ተከናውኖ አጫጭርና የረጅም ጊዜ ስልጠናዎች ተሰጥተዋል፡፡ በተጨማሪም በጀት አመቱ አፈፃፀምን መሰረት ያደረገ ግምገማዊ ስልጠና በማካሄድ የፈፃሚዎችን አቅም የማጎልበት ሥራ ተሰርቷል።

ከመደበኛ ሥራዎች አኳያም የሰው ኃይል ማሟላት፣ የሥራ አካባቢ ደኅንነት የአደጋ መከላከያና የመጀመሪያ ርዳታ መሣርያ ግዥ፣ የጸረ-ኤች አይቪ /ኤድስ ጥምረት ስበሰባ መሳተፍና ሌሎች ተያያዥ ሥራዎች ተከናውነዋል፡፡

የኤጀንሲውን አገልግሎቶች የማስተዋወቅና ግንዛቤ የማስጨበጥ ሥራዎችን በተመለከተ በሕዝብ ግንኙነት ሥራዎች አኳያ የጽሑፍ ሥራዎች፣ የቃለመጠይቅ፣ ፕሬስ ኮንፈረንስንና ፕሬስ ሪሊዝ፣ እንዲሁም መድረኮችን የማመቻቸት ሥራዎች ተከናውነዋል፡፡ በተጨማሪም ሁነቶችን የማዘጋጀትና የማስተባበር ሥራዎች መከናወናቸው በሪፖርቱ ተመልክቷል፡፡

በኤጀንሲው የሥርዓተ ጾታ ተኮር አሰራርን አጠናክሮ ከመቀጠል አኳያ የሴቶችን ተሳታፊነትና ተጠቃሚነት የማበረታታት ሥራዎች፣ ማለትም በቅጥር፣ በደረጃ እድገትና በዝውውር፣

በዝቅተኛ ደረጃ ላይ ለሚገኙት ሠራተኞት የትምህርት ዕድል ማመቻቸት፣ እንዲሁም የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራዎች ተከናውነዋል፡፡

ለኤጀንሲዉ የተፈቀደዉን በጀት ወጪ ቆጣቢና ዉጤታማ በሆነ መንገድ ስራ ላይ እንዲዉል ከማድረግ አኳያ፡- የመደበኛ፣ የካፒታል እና የፕሮግራም በጀት ሥራዎች መርሀ-ግብር ማዘጋጀት በዕቅዱ መሰረት ተከናውኗል፡፡ የስድስት ወር ዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርት በማዘጋጀት ለሚመለከታቸው አካላት እንዲደርስ ተደርጓል። የጽሕፈት መሳሪያዎች፣ የፅዳት ዕቃዎች፣ የደንብ ልብስና የሌሎች ዕቃዎች የማእቀፍ ግዥ በዕቅዱ መሠረት ተከናውኗል፡፡ ለግዥ፣ ለውሎ አበልና ለሥራ ማስኪያጃ የተፈፀሙ ክፍያዎችን ሂሳባቸውን አጣርቶ ማወራረድ በሰባት ወሩ በዕቅዱ መሠረት ተከናውኗል፡፡



የፋይናንስ፤ የንብረትና የክዋኔ ኦዲት በማድረግ የኤጀንሲው በጀት እና ንብረት ወጪ ቆጣቢ፣ ውጤታማ መሆኑንና ለታለመለት ዓላማ መዋሉን ማረጋገጥ ከሚለው ግብ አኳያ፣ ከወጪ ቀሪ የጥሬ ገንዘብ ቆጠራ ማካሄድ፣ የሰው ሀይል ቅጥር ዕድገትና ዝውውር መገምገምና አሰራሩ ደንብና መመሪያን የተከተለ መሆኑን ማረጋገጥ በሚለው በሰባት ወር ውስጥ ሙሉ ለሙሉ ተከናውኗል፡፡

የሀገሪቱን የቆዳ ሽፋን ወካይ የሆነ የሚቲዎሮሎጂ መረጃ ጥራቱን በጠበቀ ሁኔታ ለመሰብሰብ አሁን ያሉትን የተለያየ ደረጃ ያላቸውን የሚቲዎሮሎጂ ጣቢያዎች ከማሳደግ አኳያ የተከናወኑት ተግባራት፣ የሀገሪቱን የአየር ሁኔታና ጠባይ በመከታተል ጥራቱን የጠበቀና ወቅታዊ የሆነ ለሀገሪቱ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ እድገት አስተዋጽዖ የሚያደርግ የአየር ሁኔታና አየር ጠባይ ትንበያና ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ ከመስጠት አኳያ የተከናወኑት ተግባራት፣ ጥራቱንና ወቅታዊነቱን የጠበቀ የአፕላይድ ሚቲዎሮሎጂ አገልግሎት ተደራሽ ከማድረግ አኳያ፣ ለአየር ትራንስፖርት ደህንነትና ስኬታማነት አለም አቀፍ ጥራትና ደረጃውን የጠበቀ የኤሮኖቲካል ሚቲዎሮሎጂ አገልግሎት ተደራሽ ከማድረግ አኳያ፤ የሚቲዎሮሎጂ እና ተዛማጅ ሳይንስ ዘርፎች ላይ ትኩረት ያደረጉና ችግር ፈቺ የሆኑ የጥናትና ምርምር ሥራዎችን ከማካሄድ አኳያ የተከናወኑት ተግባራት በዝርዝር ቀርበዋል፡፡

የካፒታል ፕሮጀክቶች አፈጻጸም ከጣቢያዎች ማቋቋምና ማጠናከር አኳያ፣ የኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ከማደራጀት፣ የሚቲዎሮሎጂ መሣርያዎች ግዥ፣ አየቪዬሽን ሚቲዎሮሎጂ አቅም ማሳደግ አኳያ የተከናወኑት ተግባራት በሪፖርቱ ተመልክተዋል፡፡

የ7 ወሩ የፋይናንስ አጠቃቀምን በተመለከተ ኤጀንሲው በ2010 ከተመደበለት አጠቃላይ 165,000,000 ብር፣ በመደበኛው ከተመደበው ብር 75,000,000 ውስጥ በ7 ወር 40,890,000.00 ለመጠቀም ታቅዶ 37,966,908.62 በሥራ ላይ ውሏል። በካፒታል ከተመደበው በጀት ብር 60,000,000 በ7 ወር 17,660,000.00 ውስጥ 11,886,299.82 በሥራ ላይ ውሏል። ከለጋሾች በአመት ከታቀደው 30,000,000.00 ብር በ7 ወር ውስጥ 18,000,000.00 ለመጠቀም ታቅዶ 17,500,000.00 ብር በሥራ ላይ ውሏል። በአጠቃላይ በዓመቱ በመደበኛና በካፒታል 165,000,000 ብር በ7 ወር 76,550,000.00 ለመጠቀም ታቅዶ 51,603,208.44 በሥራ ላይ መዋሉ በቀረበው ሪፖርት ተመልክቷል፡፡

በቀረበው ሪፖርት ላይ ሰፊ ውይይት ከተካሄደ በኋላ ለዕለቱ በተያዘው መርሐ-ግብር መሠረት፣ አዲሱን የሠራተኞች አዋጅ የማስተዋወቅና በተጓደሉ የተለያዩ ኮሚቴዎች አባላት ምትክ ምርጫ ተካሂዶ ስብሰባው አብቅቷል፡፡

## በየክፍሉ እየተከናወኑ ያሉ ሥራዎችንና በቀጣይ አገልግሎቱን ለማሻሻል የታቀዱ ግቦችን ስኬታማ ለማድረግ ወሳኝ አቅጣጫዎች ተቀመጡ

አቅጣጫዎቹ የተቀመጡት ከ17-18/06/2010 በተካሄደው ውይይት ማጠቃለያ ላይ ሲሆን በሥራ አፈጻጸምና በአገልግሎት አሰጣጣችን ዙሪያ በየክፍሉ የተከናወኑት ተግባራት፣ የአፈጻጸም ደረጃና በአገልግሎት አሰጣጣችን መሻሻል ስላለባቸው ነገሮች የየክፍሉ ሪፖርት በቀረበበት ጊዜ ነው፡፡

የክፍል አስተባባሪዎችና ተወካዮች የአገልግሎት አሰጣጡን መግለጫ ካቀረቡ በኋላ ሰፊ ውይይት ተካሂዶ፣ በውይይቱ ጎልተው ከተነሡትና በቀጣይ ትኩረት ይሻሉ ተብሎ በበላይ አመራሩ አቅጣጫ ከተሰጠባቸው ጉዳዮች ውስጥ፣

ትንበያችን ከግለሰብ-ተኮር፣ የጋራ መርሕን ወደ ተከተለ አገባብ መቀየር እንደሚኖርብን አጽንዖት ተሰጥቶታል። ለዚህም የትንበያና ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ ዳይሬክቶሬት ከሚመለከታቸው የሥራ ክፍሎች ጋር መሥራት ይኖርበታል።

በውስን አካባቢዎች Point forecast ለመስጠት የሚያስችለው (NWP) አዲስ የተገዛውን ትልቅ ኮምፒውተር በመጠቀም ወደ ሙሉ ትግበራ ምዕራፍ በፍጥነት ሊያስገቡን በሚያስችሉን ጉዳዮች ላይ ትኩረት ተደርጎ መሥራት ይኖርብናል፡፡

በሀገራችን የወቅቶች የአየር ጠባይ ላይ ተፅዕኖ ሊያሳድሩ የሚችሉ ከዚህ ቀደም የሀገራችንን የወቅት የአየር ጠባይ ትንበያን ለመስጠት ወሳኝ ይሆናሉ ብለን ከለየናቸውና በተለምዶ ከምናውቃቸው ባሻገር በየአካባቢው ምክንያት ሊሆኑ የሚችሉ ጉዳዩችን የትንበያና ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ ዳይሬክቶሬት በተለይም በየክልል አገልግሎት ማዕከላት ሥር ከሚገኙ ባለሙያዎች ጋር ጠንካራ ትስስር በመፍጠር በነዚህ ጉዳዩች ላይ ትኩረት አድርጎ ቢሠራ ትንበያችንን ለማሻሻል ከፍተኛ አስተዋፅኦ ስለሚኖረው ለሥራው ትልቅ ትኩረት ቢሰጠው፡፡

ለአየር ሁኔታ መረጃ የተሻለ የአየር ሰዓት እንዲሰጠው ከ EBC ጋር የተጀመረው ሥራ ተጠናክሮ እንዲቀጥል የሕዝብ ግንኙነት እና ትንበያ ዳይሬክቶሬቶች በጋራ መሥራት ይኖርባቸዋል፡፡

የኤጀንሲው አገልግሎት ይበልጥ ሊሻሻል የሚችለው በጥናትና ምርምር ሲደገፍ በመሆኑ በዚህ ዘርፍ በ2010 የተጀመሩ ሥራዎች በፍጥነት መጠናቀቅ እንዳለባቸውም አቅጣጫ ተቀምጧል።

በልማት ሚቲዎሮሎጂ ዳይሬክቶሬት በቂ የሰው ሀይል የተመደበ ስለሆነ ከተለመዱ አሠራሮች ተላቀን ከወቅቱ ጋር የሚሄዱ የምክር አገልግሎቶች ተዘጋጅተው እንዲሰራጩ ቢደረግ በተለይ የENCAT መረጃዎችን ጤና ጥበቃ ሚ/ር በጣም ስለሚፈልግ፣ ከእነሱ ጋር በቅርበት ቢሠራ፤ እስከ ክልል ድረስ ሁሉም የሥራ ክፍሎች ተደጋግፈውና ተናበው ሥራቸውን ውጤታማ በሆነ መልኩ ማከናወን እንደሚጠበቅባቸው አቅጣጫ ተቀምጧል፡፡